Aqeeda

Childrens text book

አቂዳ

የልጆች ማስተማሪያ መጽሐፍ

አዘጋጅ ሙሳ ሪቻርሰን

ትርጉም፡ በአህመድ የሱፍ (የወጣቱ ተልዕኮ)

All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ
የወጣቱ ተልዕኮ የኦንላይን እትም 2010
ሰሜን ወሎ ወልድያ

ahmedyesuf29@gmail.com
+251927790323
https://youth-mission.com

የወጣቱ ተልዕኮ
አህመድ የሱፍ

Presented by: Youth-Mission
Online Amharic Islamic Books
Publishing.


بسم الله الرحمن الرحيم

ይዘት

አሏህማንእንደሆነታውቃላችሁ?.....7

ክለሳ.....8

ሁልጊዜምግበንየሚሰጠንአሏህነው።.....9

ክለሳ.....10

አሏህንየሚመስልአንድምነገርየለም.....11

ክለሳ.....12

አሏህሁሉንምነገርያቀውቃል.....13

ክለሳ.....15

ክለሳ.....17

ነብዩሙሐመድማንእንደሆኑታውቃለህ.....18

ክለሳ.....20

ነብዩሙሐመድከብዙአመትበፊትነውየሞቱት.....21

ክለሳ.....22

ሙስሊምምንእንደሆነታውቃለህ.....23

ክለሳ.....24

አንዳንድሰዎችሙስሊሞችአይደሉም.....25

ክለሳ.....27

ሙስሊሞችከሞቱበኋላወደጀነትነውየሚሄዱት.....28

ክለሳ.....30
ካፊሮችወደጀነትመሄድአይችሉም.....31
ክለሳ.....33
ወደጀነትለማይሄዱሰዎችሌላቦታአለ.....34
ክለሳ.....35
ወደጀሐነምየሚሄዱትመጥፎሰዎችብቻናቸው።.....36
ክለሳ.....38
መልካስራዎችእናሶደቃ.....39

ማስታወሻ ለመምህራን እና ለወላጆች

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ ለሆነው።

የአሏህ ሰላት እና ሰላም በነብያት መደምደሚያ እና የሰቸውን ፈለግ በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን።

ይህ መጽሐፍ የ4 አመት ልጆች ሊረዱት በሚችል መልኩ አንዳንድ መሰረታዊና ትክክለኛ የሙስሊም እምነት/አቂዳ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው። በዚህ ክፍል ከተዳሰሱ አርዕስቶች ውስጥ

- ጌታህ ማነው?
- አሏህን የሚመስል ምንም ነገር የለም?
- አሏህ የት ነው?
- አሏህ ሁሉንም ነገር ያውቃል?
- ማነው ነብይህ?
- ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በህይወት አሉ ወይስ ሞተዋል?
- አሏህ በህይወት አለ?
- ቁርአን ምንድን ነው?

- ሃይማኖትህ ምንድን ነው?
- ሙስሊም ማለት ምን ማለት ነው?
- ካፊር ማለት ምን ማት ነው?
- ጀነት ምንድን ነው?
- እዛ መድረስ የሚቻለው እንዴት ነው?
- ጀሃነም ምንድ ነው?
- ወደዛ የሚወስደው ምንድን ነው?

መምህራን እና ወላጆች እነዚህ አርዕስቶች በዚህ ክፍል በዝርዝር የተቃኙ አይደሉም። እነዚህ አርዕስቶች በዚህ ተከታታይ ትምህርት ይከለሳሉ።ልጆች እያደጉ ሲሄዱ እና ብዙ የመረዳት አቅማቸው ሲዳብር የትምህርት ደረጃቸውን ሲያሻሽሉ አርዕስቶቹ በዝርዝር የሚቃኙ እና የሚገለፁ ይሆናል። ይህን ተከታታይ መጽሐፍ በመጠቀም ልጆች ሁሉንም ባይባል እንኳ አብዛኛውን መሰረታዊ የእስልምና እምነት አስተምህሮት ጠንካራ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።

የዚህ መጽሐፍ የትኩረት ነጥብ ልጆች ስለ ኢስላም እንዲረዱ ፣ እንዲያስታውሱት ፣ አብሯቸው እንዲያድግ እና በተርቢያ እንዲያድጉ ማስቻል ነው።

ይህ ግብ እውን ይሆን ዘንድ ወላጆች እና መምህራን የልጆችን ተረድኦ መፈተሽ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ቀላል ጥያቄዎች ከየ ትምህርቱ መጨረሻ ቀርበዋል። ይሄም ልጆች የራሳቸውን መልስ የሚያስቀምጡበት ነው።መመለስ ካልቻሉ የመጀመሪያዎቹ ጥያቄዎች መልሳቸውና እንደገና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ይረዳቸዋል።

ልጆች ከትምህርት ቤት ከወላጆች ጋር ይጋብዛቸዋል። ትምህርቶቹ ያን ያህል ስለማይከብዱ የተሰጣቸውን ጥያቄዎች ያለምንም ችግር ይመልሷቸዋል ብየ አስባለሁ ኢንሻአላህ!

የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በራሳቸው መጽሐፍን ላያነቡት ወላጅ ሊፀና እንደማይችሉ አስባለሁ።ስለዚህ ወላጆች እና መምህራኖች የራሳችሁን ሚና ተጫወቱ። ነገርግን በዚህ ክፍል ማንበብ እና መፃፍ የሚችሉ ልጆች የዚህ መጽሐፍ ኮፒ ቢሰጣቸው እና በራሳቸው ቢያነቡና ቢመልሱ ጥሩ ነው።

ይህ መጽሐፍ ግቡን ይመታል ብየ ተስፋ አደርጓለሁ። አላህ የዚህን መጽሐፍ ፀሐፊና ተርጓሚ ፣ ከሷም ጋር

የሚያስተምሩትን እና የሚማሩትን በመልካም ነገሮች ሁሉ ይመንዳቸው። አሏህ ሁላችንንም በዲናችን ጠንካሮች ያድርገን።

ወንድማችሁ

አቡ አባስ ሪቻርድሰን

1422/9/20

አሏህ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

አሏህ ጌችን ነው።

ሁሉንም ሰው የፈጠረው እሱ ነው።

ዛፎች ፣ ወንዞች ፣ ተራራዎችን ፣ የፈጠረው እሱ ነው።

ሰማይን ፣ ፀሐይን ፣ ጨረቃን እና ከዋክብትን የፈጠረው እሱ ነው።

ሁሉንም እንስሳት የፈጠረው እሱ ነው።

ሁሉንም ነገር የፈጠረው አሏህ ነው።

ክለሳ

ጌታህ ማነው?

እኛን የፈጠረን ማነው?

እንስሳቶችን የፈጠረው አሏህ ነው?

ፀሐይን የፈጠረው ማነው?

ተራራዎችን የፈጠረው አሏህ ነው

ኮከቦችን የፈጠረው ማነው?

ሌላስ አሏህ የፈጠረው ምንድን ነው?

በሰማይ የሚበሩ ወፎችን የፈጠረው አሏህ ነው?

ደመናን የፈጠረው ማነው?

ሁልጊዜ ምግበን የሚሰጠን አሏህ ነው።

ጤነኛ ያደረገን እሱ ነው፡፡

እጆቻችንን እና እግሮቻችንን የሰጠን አሏህ ነው።

አይናችንን እና ጆሯችንን የሰጠን አሏህ ነው።

ምላሳችንን እና ጥርሳችንን የሰጠን እሱ ነው።

አሏህ ብዙ ነገሮችን ሰጥቶናል።

አሏህ ብዙ ነገሮችን ሰጥቶናል።

ክለሳ

ሁልጊዜ አሏህ ምግብ ይሰጠናል?

ጤነኛ ያደረገን ማነው?

አባት እና እናት የሰጠን ማነው?

ጥርሳችንን የሠጠን አሏህ ነው?

አይናችንን የሰጠን ማነው?

ሌላ አሏህ የሠጠን ነገር ምንድን ነው?

አፍንጫችንን የሠጠን አሏህ ነው?

ቤታችንን የሠጠን ማነው?

አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም!

ተራራዎችን እና ሰማይን የፈጠረው አሏህ ነው።

አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም።

ላባታችነን እና እናታችነን ፣ አህቶቻችነን እና ወንድሞቻችነን የሰጠን አሏህ ነው።

ይሄን ማድረግ የሚችል ሰው አለ

የለም! አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም

አሏህ ከሰማይ በላይ ነው

አሏህ ከሁሉም ነገር በላይ ነው

ሰብሃንአሏህ!

ከእሱ በላይ ከፍ ያለ አለ

የለም! አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም።

ክለሳ

አሏህን የሚመስል ነገር አለ?

ከአሏህ ውጭ ተራራን መፍጠር የሚችል አለ?

አሏህ የትነው ያለው?

አሏህ ከሁሉም ነገር በላይ ነው?

ከሁሉም በላይ የሆነ ምን አለ?

እዚህ ቤት ውስጥ አሏህ አለ?

አባትህ ልክ እንደ አሏህ ይመስላል?

አሏህ የሚመስል ማነው?

አሏህ ሁሉንም ነገር ያውቃል

አሏህ አሁን ምን እያደረግን እንደሆነ ያውቃል።።

አሏህ ትናንት የሰራነውን ያውቃል።።

አሏህ ነገ የምንሰራውንም ያውቃል።

አሏህ ነገ የት ቦታ እንደምንሄድ ያውቃል።

ምንም ነገር ብንሰራ አሏህ ያውቀዋል።

አሏህ ሁሉም እንስሳቶች የሚሰሩትንም ያውቃል።

የትኛውም ቦታ ላይ ብንሆን አሏህ ያየናል ይሰማናል።

አሏህ መልካም ነገር ስንናገር ይሰማናል። መጥፎ ነገርም ስንናገር ይሰማናል።

አሏህ መልካም ነገር ስንሰራ ያየናል።መጥፎ ነገርም ስንሰራ ያየመናል።

ሁሉን የሚሰማ ፤ ሁሉን የሚያይ ከአሏህ ውጭ አንድም ነገር የለም። ሁሉን የሚያይ ሁሉን የሚሰማ አሏህ ብቻ ነው።

አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም።።

አሏህ ያየኛል፣ ይሰማናል። አሏህ ያለው ከሰማይ በላይ ነው። አሏህ ከሁሉም ነገር በላይ ነው ያለው።

ሱብሃን አሏህ!

ክለሳ

ሁሉንም ነገር አሏህ ያውቃል?

ትናንት የሠራነውን ነገር አሏህ ያውቀዋል?

አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ አሏህ ያውቃል?

የምንሰራውን ሁሉ አሏህ ያል ይሰማል

አሏህ ያለው የት ነው?

አሏህ ያለው ከሰማይ በላይ ነው?

ከሁሉም ነገር በላይ የሆነው ማነው?

የምንሰራውን ነገር ሁሉ የሚያውቅ ማነው?

አሁን ቤት ውስጥ መሆናችንን አሏህ ያውቃል?

አሁን ስናወራ አሏህ ይሰማናል?

አሁን መቀመጣችንን አሏህ ያያል?

አሏህ የማያየው ወይም የማይሰማው ነገር አለንዴ?

አሏህ የማያውቃቸው ነገሮችስ አሉ?

የሆነ በሰው

مَنْ رَبُّكَ؟

ጌታህ ማነው? ብሎ ቢጠይቀህ

رَبِّيَ اللَّهُ

ጌታየ አላህ ነው ብለህ ንገረው።።

ክለሳ

مَنْ رَبُّكَ؟ ጌታህ ማነው?

ነብዩ ሙሐመድ ማን እንደሆኑ ታውቃለህ?

ነብዩ ሙሐመድ ነብያችን ናቸው።

አሏህ የላካቸው ለሁለም ህዝቦች ነው።

ነብዩ ሙሐመድ ከረዥም ጊዜ በፊት የኖሩ ሰው ናቸው።

አሏህ ለሳአቸው ቁርአንን ሰጥቷቸዋል።

ቁርአን ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

ቁርአን የአሏህ መጽሐፍ ነው።

ጥሩ ሰዎች ሁልጊዜ ቁርአን ያነባሉ።

ጥሩ ሰዎች ቁርአን ይወዳሉ። ሲነበብም መስማት ይወዳሉ።

ቁርአን በጣም ደስ የሚልና የሚያምር ነው።

ነብዩ ሙሐመድ ቁርአንን ይወዳሉ። የአሏህን መጽሐፍ ይወዳሉ።

ነብዩ ሙሐመድ ቁርአንን አዘውትረው ያነቡ ነበር።

ነብዩ ሙሐመድ ሰዎችን ስለ ቁርአን አስተምረዋል።በጣም ምርጥ የሰው ልጅ ቁንጮ ናቸው።

ጥሩ ሰዎች ልክእንደ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለመሆን ይሞክራሉ። እኛም እንደነሱ ለመሆን መሞከር አለብን።

የሆነ ሰው مَنْنَبِيُّكَ؟ ነብይህ ማነው? ብሎ ከጠየቀህ نَبِيِّيمُحَمَّدٌ ነብየ ሙሐመድ ናቸው በል።

ክለሳ

ሙሐመድ ማነው?

ጥሩ ሰው ነበሩ ወይስ መጥፎ ሰው?

ነብይህ ማነው? مَنْ نَبِيُّكَ؟

አሏህ ለነብዩ ሙሐመድ ቁርአን ሰጥቷቸዋል?

ቁርአን ማንበብ ነብዩ ይወዳሉ አይደል?

ነብዩ ሙሐመድ ስለ ቁርአን ሰዎችን አስተምራዋል?

ጥሩ ሰዎች እንደማንነው መሆን የሚፈልጉት?

ከነብዩ ሙሐመድ የተሻለ ሰው አለ?

ቁርአን ማንበብ ትወዳለህ?

ልክ እንደ ነብዩ ሙሐመድ መሆን ትፈልጋለህ?.....ለምን?

ነብዩ ሙሐመድ የሞቱት ከብዙ አመት በፊት ነው።።

ያ ማለት ማለት አሁን በህይወት የሉም፤ ሞተዋል። አሏህ አለ፡ እሱ ፈፅሞ አይሞትም። አሏህ ልክ እንደ ነብዩ ሙሐመድ ሰው አይደለም።

አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም!

ሁሉም ሰው አንድ ቀን ይሞታል ከአሏህ በቀር።።

ሰዎች ሲሞቱ መሬት ውስጥ ይቀበራሉ።

ጥሩ ሰዎች አሏህን ብቻ ያመልካሉ።

አሏህ ሁሌም ፀሎታችንን ይሰማናል።

ጥሩ ሰዎች ነብዩ ሙሐመድን ይወዳሉ ነገርግን እሳቸውን አያመልኩም።።

ክለሳ

ነብዩ ሙሐመድ በህይወት አለ?

አላህ በህይወት እንዴ ልጆች?

ነብዩ ሙሐመድ ሞተዋል እንዴ?

የሰዎች ሁሉ አለቃ ማነው?

የሞቱ ሰዎችን የትነው የምናደርጋቸው?

ፀሎታችንን አላህ ይሰማናል?

ሰዎች ነብዩ ሙሐመድን ያመልካሉ እንዴ?

ሙስሊሞች የሚያመልኩት ማንን ነው?

ነብዩ ሙሐመድ ከሰማይ በላይ ናቸው እንዴ?

አላህ ትወዳላችሁ?

የምታመልኩት አላህን ነው?

ነብዩ ሙሐመድን ትወዷቸዋላችሁ?

ነብዩ ሙሐመድን ታመልኳቸዋላችሁ?

ሙስሊም ምን እንደሆነ ታውቃለህ?

ሙስሊም ማለት አሏህን ብቻ የሚገዛ ጥሩ ሰው ነው።

አሏህ ሙስሊሞችን ይወዳቸዋል።

ሙስሊሞች አሏህን ይወዱታል።

ሙስሊሞች ነብዩ ሙሐመድን ይወዳሉ።

ሙስሊሞች ጥሩ ሰዎች ናቸው።

ሙስሊሞች እንደ ነብዩ ሙሐመድ መሆን ይፈልጋሉ ነገርግን አያመልኳቸውም።

እኛ ሙስሊሞች ነን። ሃይማኖታችን ደግሞ ኢስላም ነው።

የሆነ ሰው؟ مَادِينُكَ ሃይማኖትህ ምንድን ነው? ብሎ ቢጠይቅህ ሃይማኖቴ ኢስላም ነው በለው።

ክለሳ

ሙስሊሞች አሏህን ያመልኩታል?

ሙስሊሞች ነብዩ ሙሐመድን ያመልኩታል?

ሙስሊሞች መሆንነው የሚፈልጉት እንደማን?

ሙስሊሞች አሏህን ይወዱታል?

ሙስሊሞች ነብዩ ሙሐመድን ይወዱታል?

ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው? مَادِينُكَ؟

ሙስሊሞች ጥሩ ሰዎች ናቸው?

ሙስሊሞችን አሏህ ይወዳቸዋል?

አሏህ ትወዱታላችሁ?

ነብዩ ሙሐመድን ትወዱታላችሁ?

ሙስሊሞችንስ ትወዳላችሁ?

አንዳንድ ሰዎች ሙስሊሞች አይደሉም።

ሃይማኖታቸው ኢስላም አይደለም።

አሏህን ብቻ አያመልኩም።

እንደ ነብዩ ሙሐመድ መሆን አይፈልጉም።

እነሱ ካፊር ተብለው ይጠራሉ።

ካፊሮች (ከሃዲዎች) በጣም ክፉ ሰዎች ናቸው።

ብዙ መጥፎ ነገሮችን ይሰራሉ።

አንዳንዴ ሙስሊሞችን ለመጉዳት ይሞክራሉ።

ሙስሊሞች ካፊሮችን አይወዷቸውም።

ካፊሮች መጥፎ ሰዎች ናቸው።

የሆነ ሰው مَنْ رَبُّكَ؟ ጌታችሁ ማነው? ብሎ ቢጠይቃቸው رَبِّيَ اللَّهُ ጌታችን አለሏህ ነው ብለው አይመልሱም።



نَبِيِّيمُحَمَّدٌ ነብይህ ማነው? ተብለው ቢጠየቁ مَنْنَبِيُّكَ؟ ነብየ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው ብለው አይመልሱም።

የሆነሰው **مَادِينُكَ؟** ሃይማኖታችሁ ምንድነው? ብሎ ቢጠይቃቸው **دِينِيَاإِسْلَامٌ** ሃይማኖቴ እስልምናነው አይሉም።

ሱብሃን አሏህ!

ክለሳ

ካፊሮች አሏህን ብቻ ያመልካሉ?

ካፊር ሙስሊም ነው እንዴ?

ካፊሮች ጥሩ ሰዎች ናቸው?

ሙስሊሞች ካፊሮችን ይወዷቸዋል?

ካፊሮች እንደ ነብዩ ሙሐመድ ለመሆን ይሞክራሉ?

ካፊር ሰው ጌታየ አሏህ ነው ይላል እንዴ?

ካፊር ሰው ሃይማኖቴ እስልምና ነው ይላል?

ካፊር ሰው ነብየ ሙሐመድ ናቸው ይላል?

ካፊሮች ሙስሊሞችን ለመጉዳት ይሞክራሉ?

ካፊሮች አሏህን ይወዳሉ?

ካፊሮችን ትወዳቸዋለህ?

ማነው ጥሩ ሰው ሙስሊም ወይስ ካፊር?

ሙስሊሞች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱት ወደ ጀነት ነው

ጀነት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ

ጀነት ትልቅ የሚያምር ቦታ ነው

ሙስሊሞች ብቻ ናቸው ወደ ጀነት የሚሄዱት

ጀነት ውስጥ ብዙ የሚጠና የሚበላ ምግብ አለ

ጀነት ውስጥ ያሉ ሰዎች እንደፈለጉ ይበላሉ ይጠጣሉ።

ፊፅሞ ወደ መታጠቢያ ክፍል መሄድ አይሄዱም።

ጀነት ውስጥ የማር እና የወተት ወንዞች አሉ።

ጀነት ውስጥ የሚጣፍጡ የሚጥሙ አትክልት እና ፍራፍሬዎች አሉ።

ጀነት ውስጥ ያሉ ሰዎች አሏህን ያያሉ። በጣም ይደሰታሉ።

አሏህን ማየት ትፈልጋላችሁ?

አዎ ሁላችንም ማየት እንፈልጋለን።

ነገርግን ጀነት ካልገባን በቀር አሏህን አናየውም።

ሰዎች የሚወዱትን ነገር ሁሉ ጀነት ውስጥ ያገኛሉ። በጣም በጣም ይደሰታሉ።

ክለሳ

ሙስሊሞች ጀነት የሚገቡት መቼ ነው።

ጀነት ትልቅ ቦታ ነው

ጥሩ ሰዎች ጀነት ውስጥ ይኖራሉ

ሙስሊሞች ጀነት ውስጥ ይበላሉ

ሰዎች ጀነት ውስጥ ወደ መታጠቢያ ክፍል ይሄዳሉ

አሏህን ያያሉ ጀነት ውስጥ ያሉ ሰዎች

ጀነት ውስጥ ዛፎች አሉ

ጀነት ውስጥ ያሉ ሌሎች ነገሮች ምንድን ናቸው።

ሁሉም ሰው ጀነት ውስጥ ይደሰታል

ነብዩ ሙሐመድ ጀነት ውስጥ ይኖራሉ

ወደ ጀነት ካልሄድን አሏህን ማየት እንችላለን

ካፊሮች ወደ ጀነት መሄድ አይችሉም

ወደ ጀነት መሄድ ከፈለጋችሁ ጥሩ ሙስሊሞች መሆን አለባችሁ

ወደ ጀነት ለመሄድ ደግሞ አሏህ እና ነብዩ መሐመድን መታዘዝ አለባችሁ

እንዲሁም ወደ ጀነት ለመሄድ እናት እና አባታችሁን መታዘዝ አለባችሁ

ወደ ጀነት ለመሄድ ጥሩ ነገሮችን መስራ አለባችሁ

ወደ ጀነት ለመሄድ ጥሩ ነገሮችን መናገር አለባችሁ

ወደ ጀነት መሄድ ከፈለጋችሁ ሙስሊሞችን መርዳት አለባችሁ። እነሱን መጉዳት አይኖርባችሁም።

ወደ ጀነት መግሄድ ከፈለጋችሁ ለሰዎች ሁሉ ደግ እና አዛኝ መሆን አለባችሁ። ካፊሮች እንኳ ቢሆኑ።

አንድ ሰው ወደ ጀነት አይሄድም፤ አሏህ እንዲሄድ ካልፈቀደለት በቀር

እናም አሏህ ጀነት እንዲያስገባን እሱን መለመን አለብን።

አሏህ ሆይ! ወደ ጀነት እንድንሄድ አድርገን። አሏህ ሆይ! ወላጆቻችን ጀነት እንዲገቡ አድርግልን።

ክለሳ

ወደ ጀነት ካፊሮች መሄድ ይችላሉ።

ወደ ጀነትየሚሄደው ማነው

ሰዎች ወደ ጀነት መሄድ ከፈለጉ ለሌሎች ሙስሊሞች ደግና አዛኝ መሆን አለባቸው።

ወደ ጀነት እንድንሄድ አሏህ ከፈቀደልን መሄድ እንችላለን

ወደ ጀነት ለመሄድ ሌላ ምን ማድረግ አለብን።

ሁሉም ሰው ወደ ጀነት ይሄዳል

ጀነት ለመግባት ማንን ነው የምንጠይቀው

ወደ ጀነት ለማይሄዱ ሰዎች ሌላ ቦታ አለ

ቦታው በጣም አስከፊ እና የሚያሰቅቅ ነው። ጀሃነም ተብሎ ይጠራል።

ጀሃነም በውስጡ ያሉ ሰዎችን የሚያቃጥል ትልቅ የእሳት ጉድጓድ ነው። ወደ ጀሃንም የሄዱ ሰዎች በእሳት ይቃጠላሉ።

ወደ ጀሀነም መሄድ የሚፈልግ አንድም ሰው የለም። ጀሐነም የሰዎችን ቆዳ ያቃጥላል። ጀሐነም በጣም የሚያስጠላ ቆሻሻ ቦታ ነው።

ጀሐነም ውስጥ የሚያስጠላ መርዛማ ዘቁም የተባለ ዛፍ አለ። ዘቁም ሰዎች እንዲታመሙ የሚያደርግ መርዛማ ፍሬ አለው። ጀሐነም ውስጥ የሚበሉት ይሄ ነው።

ጀሐነም ውስጥ ወሃ በጣም ይጠማቸዋል። የሚጠጡት የፈላ ሙቅ ውሃ ነው። ጀሐነም ውስጥ ሰዎች ፈፅሞ ደስተኛ አይሆኑም።

ክለሳ

ደስ የሚል ቦታ ነው ጀሃነም

ሰዎች ወደ ጀሐነም መሄድ ይፈልጋለ እንዴ

ሰዎች ጀሐነም ውስጥ ይቃጠላለ

ጀሐነም ውስጥ ዛፍ አለ

ጀሐነም ውስጥ ያለ ሰዎች የሚበለት ምንድን ነው

ዘቁም ምንድን ነው

ሰዎች ጀሐነም ውስጥ የሚጠጡት ምንድን ነው

ጀሐነም ውስጥ ያለ ሰዎች ደስተኛ ናቸው

ጀሐነም ውስጥ ያለ ሰዎች ይጠማለ

የፈላ ውሃ ሰዎች መጠጣት ይፈልጋለ ብላችሁ ታስባላችሁ

ዘቁም ተብሎ ከሚጠራው ዛፍ ፍሬ መብላት የሚፈልግ ማነው

ወደ ጀሐነም መሄድ ትፈልጋላችሁ

ወደ ጀሐነም የሚሄዱት መጥፎ ሰዎች ብቻ ናቸው።

ሁሉም ካፊሮች ወደ ጀሐነም ይሄዳሉ። ለዘላለሙ እዛው ይኖራሉ።

ምክኒየቱም አሏህን አይታዘዙም፤ ሙስሊም እንዲሆኑ ስንነግራቸው

አንዳንድ ሙስሊሞችም ወደ ጀሐነም ይሄዳሉ።

ምክኒያቱም መጥፎ ነገሮችን ይሰራሉ።

ነገርግን እንደ ካፊሮች ለዘላለሙ እዛው አይኖርም።

አሏህ ሁሉንም ሙስሊሞች ከጀሐነም አውጥቶ ጀነት ውስጥ ያስገባቸዋል።

ወደ ጀሐነም መሄድ አይፈለግም ለትንሽ ደቂቃ እንኳ ቢሆን

መሄድ የምንፈልገው ወደ ጀነት ነው።

ስለዚህ ደግሞ ጥሩ ሙስሊሞች እና አሏህን ታዛዥ መሆን አለብን።

ነብዩ ሙሐመድ እና ቤተሰቦቻችንን መታዘዝ ይኖርብናል።

መጥፎ ነገር ከተናገርን ወይም መጥፎ ነገር ከሰራን አሏህ ጀሐነም ውስጥ ሊያስገባን ይችላል።

ወደ ጀሐነም ከመሄድ አሏህ እንዲጠብቀን እሱን መለመን አለብን።

ወደ ጀሐነም ከመሄድ የሚያድነን አሏህ ብቻ ነው።

አሏህ ሆይ! ጀሐነም ውስጥ አታስገባን

አሏህ ሆይ! ወላጆቻችንን ጀሐነም ውስጥ አታስገባብን

አሏህ ሆይ! ሁላችንንም ጀነት አስገባን።

ክለሳ

ጥሩ ሰዎች ወደ ጀሐነም ይሄዳሉ እንዴ

ካፊሮች ወደ ጀሐነም ይሄዳሉ

አንዳንድ ሙስሊሞችስ ወደ ጀሐነም ይሄዳሉ

ካፊሮች ወደ ጀሐነም የሚሄዱት ለምንድን ነው።

ካፊሮች ጀሐነም ውስጥ የሚኖሩት ለምን ያህል ጊዜ ነው።

ሙስሊሞች ወደ ጀሐነም ቢሄዱ እዛው ለዘላለም ይኖራሉ

አንዳንድ ሙስሊሞች ወደ ጀሐነም የሚሄዱት ለምንድን ነው

ወደ ጀሐነም ከመሄድ ሊያድነን የሚችለው ማነው

ሙስሊም መልካም ነገሮችን ብቻ ከሰራ ወደ ጀሐነም ሊሄድ ይችላል

ወደ ጀሐነም መሄድ የሚፈልግ ሰው አለ

ወደ ጀሐነም ላለመሄድ ምን መስራት አለብን

መልካም ስራዎች እና ሶደቃ

ደካሞችን መርዳት

መልካም ነገር መናገር

መጥፎ ነገር መንገድ ላይ ማንሳት

ብዙ መልካም ስራዎችን እና የሶደቃ ስራዎችን እስከቻላችሁት ድረስ ፃፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከዚህ በመጨመር እንደማስታወሻ ተጠቀሙበት። ኢንሻ አሏህ!


رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ
أَنْتَ السَّمِيعُ العَلِيمُ

ማንኛውም አይነት ሃሳብ አስተያየት ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.com ይጎብኙና መልዕክት ያስቀምጡልን። ጀዛኩሙላህ ኸይረን ከሲረን!